# የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የካሣ ድርድር እና አከፋፈል መመሪያ ቁጥር 46/2013

## የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የካሣ ድርድርና አከፋፈል መመሪያ ቁጥር 46/2013

# ክፍል አንድ
# አጠቃላይ ድንጋጌ

## አንቀፅ 1
## አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የካሣ ድርድርና አከፋፈል መመሪያ ቁጥር 46/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## አንቀፅ 2
## ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1.1. "ተቋሙ" ወይም ‹ድርጅቱ› ማለት በአዋጅ 25/1984 እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ. 303/2008 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሲሆን ተቋሙን የሚወርሱ ወይም መብትና ግዴታው የሚተላለፍላቸው ተተኪዎችንም ይጨምራል፤

1.2. "ካሳ ኮሚቴ" ማለት በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አደረጃጀት ሥር በሚገኙት ሪጅኖች እና ዲስትሪክቶች ላይ በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱ አባለት ተዋጽኦ የሚቋቋም የካሳ ኮሚቴ ነው፤

1.3. "ካሳ ጠያቂ ወይም ቅሬታ አቅራቢ" ማለት ድርጅቱ በባለቤትነት በሚያስተዳደረው የሃይል ማስተላለፊያ መስመር እና ተጓዳኝ እቃዎች አማካይነት በንብረት፣ በአካል እና በህይወት ላይ ጉዳት ደርሷል በማለት የካሳ ክፍያ የሚያቀርብ ሰው ሲሆን ህጋዊ ወኪሎችንም ይጨምራል፤

2.4 "በንብረት ላይ የሚደርስ አደጋ" ማለት በኢትዮጵያ የንብረት ህግ መሰረት በአንድ ሰው ይዞታ ወይም ባለቤትነት ስር በሚገኝ የኤሌክትሮኒክስ፤የቤት ፤ የተሽከርካሪ፤ እንስሳት፤እና የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎች ወዘተ.. ላይ በኤሌክትሪክ አደጋ ምክንያት የሚደርስ ጉዳት ነው፤

2.5 የስራ ላይ አደጋ ማለት፡- አንድ የተቋሙ ሰራተኛ በስራ ላይ እያለ የሚደርስበት አደጋ ነው፤

2.6 "ሦስተኛ ወገኖች" ማለት ከድርጅቱ አሰራር ፤ቁጥጥር እና ተግባር ውጪ በሰው ሰራሽ መንስኤዎች ምክንያት የኤሌክትሪክ አደጋ ወይም ሌሎች ጉዳቶችን የሚያደርሱ አካላት ሲሆኑ ሙያዊ ጥፋት የፈጸመ የድርጅቱን ሰራተኛም ይጨምራል፡፡

2.7 ሰራተኛ ማለት በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 4 መሰረት ከአሰሪው ጋር የስራ ውል ያለው ግለሰብ ሲሆን ስራ መሪንም ይጨምራል፤

2.8 ርትእ ማለት የቀረበውን የካሳ ጥያቄ በፍ/ህ/አንቀጽ 2099 እና 2103 መሰረት የደረሰውን ጉዳት በበቂ ማስረጃ እና በተጨባጭ ስሌት ተመርኩዞ ማስላት አስቻጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ኮሚቴው የህሊና ፍርድ/ውሳኔ/ የሚሰጥበት አግባብ ነው፡፡

2.9 አማካኝ በህይወት የመኖር ጣሪያ ማለት፡- ብሄራዊ እስታቲክስ በየጊዜው በጥናት የሚያወጣው የኢትዮጵያውያን አማካይ በህይወት የመኖር ጣሪያ ሲሆን ለካሳ ስሌት ጥቅም ላይ የሚውል አማካኝ እድሜ ጣሪያ ነው፡፡

2.10 "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም የህግ ሰውነት ያለው ነው፡፡

## አንቀፅ 3

## <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆነው፡-

3.1 የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በሚያስተዳድራቸው የሃይል ማሰራጫ መስመሮችና አውታሮች አማካኝነት በሚደርስ የኤሌክትሪክ ጉዳት፤

3.2 በተቋሙ ውስጥ በሰራተኛነት ተቀጥረው በስራ ላይ በሚገኙና ተቋሙ የመድህን ሽፋን ባልገባላቸው ሰራተኞች ላይ በሚደርስ የስራ ላይ አደጋ፤

3.3 ከኤሌትሪክ አደጋ ውጭ ባሉ ድርጅቱን ተጠያቂ በሚያደርጉ ሌሎች የፍታብሄር ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የሚኖረው ሲሆን ድርጅቱ የመድህን ሽፋን በገባላቸው ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፤

3.4 የኢንሹራንስ ሽፋን በሌላቸው የድርጅቱ ንብረቶች ላይ አደጋ ወይም ጉዳት በሚያደርሱ አካላት ላይ፤

3.5 ሶስተኛ ወገኖች በድርጅቱ ንብረት ላይ ወይም የኤሌክትሪክ አደጋ በመፍጠር በሌላ ሰው ንብረት፣ አካልና ህይዎች ላይ በሚደርሱት አደጋዎች ላይ፤

3.6 የድርጅቱ ደንበኞች ከቆጣሪ በኋላ በመኖሪ ቤቶችና በድርጅቶቻቸው ውስጥ በሚዘረጉት የኤሌትሪክ መስመር አማካይነት በሚደርሱ የኤሌትሪክ አደጋዎች ላይ ተፈፃሚነት የለውም፤

3.7 ከላይ በአንቀፅ 3.1 እንደተጠበቀ ሆኖ ከድርጅቱ ፍቃድ እና እውቅና ውጪ ህገወጥ በሆነ መልኩ ህገ-ወጥ መስመር ሲዘረጉ ወይም የኤሌትሪክ ሀይል ሲጠቀሙ በሚደርስ አደጋ ላይ ተፈፃሚነት የለውም፡፡

## አንቀፅ 4

## ዓላማ

የዚህ መመሪያ አላማ፡-

4.1 በተቋማችን የእለት ተእለት የስራ እንቅስቃሴ ወቅት በሚያጋጥሙ አደጋዎች ወይም በሚደርሱ ጉዳቶች ምክንያት ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ለተጎጂዎች ተገቢውን ካሳ መፈፀም ለማስቻል፤

4.2 በተለያዩ ምክንያቶች በተቋሙ ንብረት ላይ ጉዳት ወይም አደጋ ከሚያደርሱ አካላት ጋር በመደራደር የተቋሙን ጥቅም ማስከበር፤

4.2 ቅሬታ አቅራቢዎች በፍርድ ቤት በሚያቀርቡት ክስ ምክንያት የሚባክነውን ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ በመቆጠብ ለቅሬታ አቅራቢዎች ቀልጣፋ እና ፍትሀዊ ውሳኔ ለመስጠት፤

4.3 የድርጅቱ የካሳ አከፋፈል ስርዓት ፍትኃዊነትና ወጥነት ያለው እንዲሆን ለማስቻል ነው፡፡

## አንቀፅ 5

## <u>የመመሪያው ዋና ዋና መርሆች</u>

5.1. የካሳ ክፍያ ተፈጻሚ የሚሆነው በሃገሪቱ ህጎች መሠረት ተቋሙን ኃላፊ የሚያደርግ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፤

5.2. ከካሳ ጥያቄ ጋር የሚቀርቡ ማስረጃዎች በቂ እና ተቀባይነት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፤

5.3. የሚሰጡ ውሳኔዎች ህግን ስነምግባርን እና ይህን መመሪያ መሰረት ያደረገ መሆን ይገባዋል፤

5.4. በቀረቡት የካሳ ክፍያ ቅሬታዎች ዙሪያ ተቋሙ የመድን ሽፋን ካለው ቅሬታው በመድን ሰጪው በኩል እንዲታይ ይደረጋል፤

5.5. የደረሰውን ጉዳት መጠን በበቂ ማስረጃ እና በተጨባጭ ስሌት ማረጋገጥ አዳጋች በሚሆንበት ጊዜ የርትዕ ካሣ አከፋፈል ስርአት ተፈፃሚ ይደረጋል፤

5.6. ካሳ ለመክፈል የሚያስችል በቂና አሳማኝ ምክንያት ባለመቅረቡ ወይም በተወሰነው ካሳ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያላው አካል ጉዳዩን ስልጣን ላለው ፍርድ የማቅረብ መብት አለው፡፡

# ክፍል ሁለት

## <u>የካሳ ጥያቄ አቀራብና ውሳኔ አሰጣጥ</u>

## <u>አንቀጽ 6</u>

## <u>የጉዳት ካሳ ቅሬታ አቀራረብ ስርአት</u>

6.1 ጉዳት ደርሶብኛል የሚል ቅሬታ አቅራቢ ቅሬታውን በየደረጃው ለሚገኘው የግሪቫንስ ክፍል አደጋው/ ጉዳቱ/ እንደተከሰተ የደረሰበትን ጉዳት በፅሁፍ በ15 ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል፤

6.2 በአንቀፅ 6.1 እንደተቀመጠው ከአቅም በላይ በሆነ ችግር በ15 ቀናት ውስጥ በፅሁፍ ማቅረብ ያልቻለ አቤቱታ አቅራቢ በቀጣይ 15 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን በአካል በፅሁፍ ማቅረብ አለበት፤

6.3 የግሪቫንስ ስራ ክፍል የቀረበለትን ቅሬታ ተቀብሎ ለተቋሙ ስራ አስፈፃሚ /ሃላፊ/ ያቀርባል፤

6.4 ቅሬታ የቀረበለት ስራ አስፈፃሚ /ሃላፊ/ ጉዳዩን አይቶ ሲያምንበት ወደ ካሳ ድርድር ኮሚቴው ይመራዋል፡፡

## አንቀፅ 7

## የካሳ ኮሚቴ አደረጃትና አሰራር

7.1. የካሳ ኮሚቴው አምስት አባላት የሚኖሩት ሲሆን በኮርፖሬት/በሪጅን/ ዲስትሪክት ደረጃ ይቋቋማል፤

7.2. የካሳ ኮሚቴው አባላት በተቋሙ ውስጥ ቢያንስ ለሁለት አመት ያገለገሉ መሆን ይኖርባቸዋል፤

7.3. በአንቀፅ 7.2 የተጠቀሰውን የአገልግሎት ጊዜ የሚያሟላ ሰራተኛ ከሌለ ብቃት ያላው ሌላ ሰራተኛም ቢሆን በአባልነት ሊሳተፍ ይችላል፤

7.4. የኮሚቴው የቆይታ ጊዜ ሁለት አመት ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ ለተጨማሪ ሁለት አመት ሊራዘም ይችላል፤

7.5. የካሳ ኮሚቴው አባላት በአንቀፅ 7.6 ከተመከቱት ስራ ክፍሎች በሚመለመሉ የስራ መሪዎች ወይም ባለሙያዎች የሚወከል ሲሆን የኮሚቴ አባላቱ በአስገዳጅ ምክንያት ስብሰባው ላይ መሳተፍ ካልቻሉ በምትካቸው ተዛማጅነት ካላቸው ክፍሎች ሌላ አባል መመደብ ይቻላል ፤

7.6. የካሣ ድርድር ኮሚቴ በኮርፖሬት፤ ሪጅንና ዲስትሪክት ደረጃ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩ የስራ ክፍል የተሰየሙ ሰራተኞችን በአባልነት አካቶ ይቋቋማል፡፡

1. ኮንሱመር ግሪቫንስ እና ሪድሬሳል ኃላፊ ................................. ሰብሳቢ
2. ዲስትሪቡሽን፤ኮንስትራክሽን ኦፐሬሽን እና ሜይቴይናንስ/ ቴክኒክ ባለሙያ/
2. ሕግ አገልግሎት ........................................................ አባል

4. የአካባቢ የጤና እና ደህንነት ..............................................አባል

5. የለውጥና መልካም አስተዳደር ................................ አባልና ጸሃፊ

7.7 ከላይ የተገለጹት ስራ ክፍሎች በዲስትሪክት ደረጃ ያልተዋቀሩ ከሆነ ከተዛማጅ ስራ ክፍሎች ማሟላት ይቻላል፡፡

## አንቀፅ 8

## የኮሚቴው ተግባር እና ኃላፊነት

8.1 ኮሚቴው ከዋና ስራ አስፈፀሚ፣ የሪጅን ም/ዋ/ስ/ አስፈጻሚ፣ ዲስትሪክት ሃላፊ የተመራለትን ቅሬታ ከህግ እና ከዚህ መመሪያ አንፃር ተቋሙን ተጠያቂ የሚያደርግ መሆን አለመሆኑን አጣርቶ በመወሰን ጉዳዩን ማየት ይጀምራል፣

8.2 ኮሚቴው የቀረበለትን ቅሬታ አግባብነት ከሕግ እና ከማስረጃ አንፃር አይቶ የውሳኔ ሃሳብ ለማቅረብ እንዲቻለው እና ብቁ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖረው የራሱ የስራ አፈጻጸም ትጋት እና ስነምግባር ሊኖረው ይገባል፣

8.3 ኮሚቴው የካሳ ጥያቄን ተፈፃሚ ከሚሆኑ የፍትሐብሔር ሕግ፣ የቤተሰብ ህግ፣ አሠራና ሠራተኛ ሕግ፣ የንግድ ሕግ፣ የድርጅቱ ህብረት ስምምነት፣ የሰበር ውሳኔዎች የኢነርጂ አዋጅ 810/2006፣ እና ማናቸውንም አግባብነት ካላቸው የሀገሪቷ ህጎች ጋር በማገናዘብ መመርመር አለበት፡፡

8.4 ኮሚቴው ኃላፊነቱን በአግባቡ መወጣት እንዲችል ከሕግ ፣ከቴክኒክ፣ ከመረጃ አስተዳደር ወይም ሌሎች ከጉዳዩ ጋር ግንኙት ያላቸው የሥራ ክፍሎች ወይም ሦስተኛ ወገኖችን በማሰጠራት መረጃ እና ሙያዊ አስተያየት እንዲሰጡ ወይም በአካል እንዲገኝ በማድረግ የጠራ ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግ ይችላል፣

8.5 የቀረበው ቅሬታ ከህግ እና ማስረጃ አንጻር ተቋሙን በኃላፊነት የሚያስጠይቅ መሆን አለመሆኑን መርምሮ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

8.6 ኮሚቴው የቀረበለትን ቅሬታ አይቶ በስልሳ ቀናት ውስጥ የውሳኔውን ሀሳብ በአንቀፅ 6.4 መሰረት ትእዛዝ ለሰጠው ሃላፊ ማቅረብ ይኖርበታል ፡፡

8.7 በኮሚቴው የቀረበው ውሳኔ ሃሳብ በአንቀፅ 10 መሰረት የሚጸድቅ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 9

## ውሳኔ ድምፅ አሰጣጥ (Voting)

9.1 የኮሚቴው ውሳኔ በድምፅ ብልጫ የሚወሰን ይሆናል፡፡ በድምጽ የተለየው አባል ምክንያቱን በፅሁፍ እንዲገልፅ ተደርጎ በውሳኔው ላይ ይሰፍራል፤

9.2 የውሳኔ ድምፅ እኩል በእኩል በሚሆንበት ጊዜ ሰብሳቢው ድምፁን የሰጠበት ውሳኔ የሚፀና ይሆናል፡፡

9.3 የኮሚቴው አባላት 2/3(ሁለት ሶስተኛው) ባልተገኙበት የሚተላለፍ ውሳኔ ተቀባይነት የለውም፡፡

9.4ኮሚቴው ባልተሰበሰበት በግለሰብ የኮሚቴ አባል ወይም በማናቸውም አካል የሚሰጥ ውሳኔ ሃሳብ ተቀባይነት የለውም፡፡

## አንቀፅ 10

## የውሳኔ ሃሳብን ስለማፅደቅ

10.1ኮሚቴው የቅሬታ አቅራቢውን አቤቱታ አጣርቶ እስከ ብር 250 ,000(ሁለት መቶ ሃምሳ ሺ. ብር) ድረስ የሚያቀርበው የክፍያ የውሳኔ ሃሳብ ለክልሉ ስራ አስፈጻሚ ቀርቦ ሲጸድቅ ተፈጻሚ ይሆናል፤

10.2 ኮሚቴው ከብር 250 ,000(ሁለት መቶ ሃምሳ ሺ. ብር በላይ የሚያቀርበው የክፍያ የውሳኔ ሃሳብ ለአገልግሎቱ ዋና ስራ አስፈጻሚ ቀርቦ ሲጸድቅ ተፈጻሚ ይሆናል፤

10.3 ከብር 500,000 በላይ የሚያቀርብ የካሳ ክፍያ የውሳኔ ሃሳብ በዚህ መመሪያ ሊስተናገድ አይችልም፡፡

10.4 ከላይ በአንቀፅ 10.1 እና 10.2 በተመለከተው መሰረት በየደረጃው የሚገኙ ኃላፊዎች ከኮሚቴ የቀረበውን ውሳኔ ሃሳብ በደረሳቸው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለባቸው፡፡ ኃላፊወች የውሳኔ ኃሳቡን የማፅደቅ፤ የማሻሻል፤ የመሻር ስልጣን አላቸው፡፡

10.5 ኮሚቴው የሚያቀርበው የውሰኔ ሃሳብ በቅሬታ አቅራቢው የቀረቡ አቤቱታና ማስረጃዎች እና ኮሚቴው ያሰባሰባቸውን እና ያያቸውን ማስረጃዎችና የኮሚቴውን ቃለ ጉባኤ ግልባጭ በማያያዝ መሆን አለበት፡፡

## አንቀፅ 11

## <u>የማስረጃ አቀራረብ፤ ማጣራት እና ምዘና ስነ-ስርአት</u>

11.1 በማናቸውም መልኩ የኤሌክትሪክ አደጋ እንደደረሰ መስመሩን በቅርበት የሚያስተዳድረው አገልግሎት መስጫ ማእከል በሶስት ቀናት ውስጥ ሶስት አባላትን የያዘ የቴክኒክ ቡድን በቦታው መላክና የአደጋ ሁኔታ ሪፖርት መያዝ አለበት፡፡

11.2 ከላይ በአንቀፅ 11.1 መሰረት የሚቀርብ የአደጋ ሁኔታ ሪፖርት በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ለዲስትሪክት ኃላፊው መላክ አለበት፤

11.3 የዲሰትሪክት ሃላፊው የቀረበው ሪፖርት ያልተሟላ፤አጠራጣሪና ግልፅነት የጎደለው ነው ብሎ ከተረዳ የህግ ባለሙያውን ጨምሮ ሶሰት ዓባላት ያሉት የቴክኒክ ቡድን ከዲሰትሪክቱ በቦታው በመላክ ተጨማሪ የማጣራት ስራ መስራት አለበት፡፡

11.4 ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በወቅቱ የደረሰውን የኤለክትሪክ አደጋ በተቋሙ ባለሙያዎች ቡድን ማጣራት ካልተቻለ ኮሚቴው የቀረበውን ቅሬታ መሰረት በማድረግ አደጋው በተፈጠረበት አካባቢ በሚገኘው ፖሊስ ጣቢያና የአስተዳደር አካላትና ነዋሪዎችን በአደጋው ሁኔታ ላይ ያላቸውን መረጃና ማስረጃ መቀበልና ማጣራት ያስፈልጋል፡፡

11.5 አደጋው የደረሰው በኤሌክትሪክ መገልገያ እቃዎች ላይ ነው ተብሎ ሲቀርብ እውነተኛነቱ በባለሙያዎች መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

11.6 በኤሌክትሪክ መገልገያ እቃዎች ላይ አደጋ ደረሰ ተብሎ ሲቀርብ አቤቱታ አቅራቢው አደጋ የደረሰባቸውን እቃዎች በባለሙያ እንዲታዩ ትብብር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

11.7 ኮሚቴው በንብረቱ ባለቤትነት፣ ተዛማጅ ማስረጃዎች እና ምስክሮች ላይ ጥብቅ የሆነ ማጣራት እና ምርመራ ማካሄድ አለበት፤

11.8 የቀረቡት የሰው ምስክሮች በሚሆኑበት ጊዜ ኮሚቴው የምስክሮቹን ማንነት እና የምስክርነት ቃላቸውን በተገቢው መንገድ ማጣራት አለበት፤

11.9 ኮሚቴው በሚያደርገው ማጣራት የቀረበው ማስረጃ ሀሰተኛ መሆኑን ካረጋገጠ ቅሬታው ውድቅ እንዲሆን ያደርጋል፤

11.10 ኮሚቴው በቀረበው ማስረጃ መሰረት አመልካች ያጣውን ትክክለኛ ጥቅም ማስላት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ ጉዳዩ በርትዕ ውሳኔ እንዲያገኝ ያደርጋል፤

11.11 የቀረቡትን የሰነድ ማስረጃዎች እውነተኛነት ማጣራት ካስፈለገ ከሚመለከተው ተቋም ጋር መረጃ ልውውጥ በማድረግ ማጣራት አለበት፡፡

11.12 በኤሌክትሪክ አደጋ የደረሰውን አደጋ በተመለከተ ለኮሚቴው ከሚሰጠው ማስረጃ ውጭ በተለያዩ ስራ ክፍሎችና ባለሙያዎች የፅሁፍ ማስረጃ መስጠት ፈፅሞ የተከለከለ ነው፡፡

11.13 ከኤሌክትሪክ አደጋ ውጭ የሚቀርቡ የካሳ ጥያቄዎችን ኮሚቴው አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎችና ምስክሮችን በመስማት ተገቢውን የውሳኔ ሃሳብ መስጠት አለበት፡፡

# ክፍል ሶስት

# የካሳ አከፋፈል ቀመር ሁኔታ

## አንቀፅ 12

## የአካል ጉዳት እና የሞት ካሣ ክፍያ የስሌት ዘዴ

### 12.1 የአካል ጉዳት ካሣ ክፍያ ስሌት

12.1.1 የአካል ጉዳት ደርሶብኛል በማለት የካሣ ክፍያ አቤቱታ ያቀረበ ተጎጂ ያቀረበው አቤቱታ ህጋዊ እና የፍሬ ነገር ተገቢነት በኮሚቴው ተረጋግጦ ተቀባይነት ሲያገኝ ለካሳው ስሌት መነሻ የሚሆነው በሕክምና ቦርድ ደረሰ ተብሎ የተረጋገጠው የአካል ጉዳት መጠን ነው፡፡

12.1.2 በህክምና ቦርድ ተረጋግጦ የቀረበው ጉዳት ከፊል ቋሚ ሲሆን በፐርሰንት ምን ያህል የመስራት ችሎታ እንዳጣ ታሳቢ ማድረግ አስፈላጊ ከመሆኑም

በላይ በሙያው ወይም ቀድሞ ይሠራው የነበረውን ሥራ ለመስራት ምን ያህል እንቅፋት እንደሚሆንበት ታሳቢ ሊደረግ ይገባል፡፡

13.1.3 የደረሰበት የአካል ጉዳት በሚያከናውነው (ሙያው ) ስራ ላይ ተፅዕኖ የማይፈጥርበት ከሆነ የሞራል ካሳ እንዲከፈለው እና የህክምና ክፍያ ወጪ እንዲተካለት ወይም እንዲፈጸምለት ሊወሰን ይችላል፤

13.1.4 በተጎጅው አካል ላይ የደረሰው ሙያውን (ሥራውን) ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል በቋሚነት ለመስራት የማያስችለው ከሆነ የካሣ አሠላሉ የሚሰራው በማስረጃ የተረጋገጠ የወር ገቢ (ደመወዝ) X 12 X ቀሪ የጡረታ እድሜ ጣሪያ (60 - የሠራተኛው እድሜ) X በህክምና ቦርድ በፐርሰንት የተረጋገጠው የጉዳት መጠንን በመጠቀም ይሆናል፤

13.1.5 የአካል ጉዳት የደረሰበት ሰው ገቢ ካልታወቀ ወይም ማስረጃ ካልቀረበ የሚሰራው ሥራ የሥራ ባህሪው የሚኖርበት አካባቢ የሥራ እና የሥራው ክፍያ መጠን ታስቢ በማድረግ በውል ውጪ ህጉ በተደነገገው የርትዕ ክፍያ ስርአት መሰረት ይሆናል፤

13.1.6 የአካል ጉዳት የደረሰበት ሰው ስራ እና ገቢ የሌለው በሆነ ጊዜ የካሣ ክፍያው በውል ውጪ ህጉ በተደነገገው የርትዕ ክፍያ ስርአት መሠረት በኮሚቴው ተወስኖ ድርድር ይደረጋል፡፡

13.1.7 ለጉዳቱ መከሰት የተጎጂው አስተዋፅኦ ካለበት በፍ/ህጉ እንቀጽ 2098 መሰረት ይህንኑ ያገናዘበ የካሳ ድርድር መደረግ አለበት፡፡

## አንቀፅ 14

## የሞት ጉዳት ካሣ ክፍያ ስሌት ዘዴ

14.1 በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር (2095)(2) መሰረት በሞት አደጋ ካሣ የመጠየቅ መብት ያላቸው የሚች ባለቤት፤ ወላጆቹ እና ልጆቹ ብቻ ናቸው፤

14.2 በአንቀፅ 14.1 ላይ በተገለጸው መሰረት የሚከፈላቸው ሰዎች በቀለብ መልክ ሆኖ ሥራ ሰርቶ እራሱን ለማስተዳደር የማይችልና ችግረኛ ሲሆኑ ብቻ ነው፡

14.3 ካሳ ጠያቂ በቀለብ መልክ ከሌላ ምንጭ የሚያገኙት ክፍያ ቢኖራቸውም ተገቢውን ካሳ ከማግኘት የሚያግዳቸው የለም፤

14.4 በአንቀፅ 14.1 አሥራ ስምንት ዓመት ያልሞላቸው ልጆች ወይም በእርጅና ምክንያት ሥራ መስራት የማይችሉ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ፤

14.5 ካሳ ጠያቂ ቀለብ የሚቆረጥለት እድሜው 18 አመት እስኪሞላው ብቻ በማገናዘብ የሚሰላ ስሌት ይሆናል፤

14.6 ለካሳ ጠያቂው የቀለብ ክፍያው የሚፈጸመው ሟች ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ ጡረታ ሊወጣ የሚችልበት የእድሜ ጣሪያ ድረስ ብቻ ነው፡፡

14.7 የቀለብ ክፍያው በየጊዜው ከመፈፀም ይልቅ ሊከፈል የሚገባውን ክፍያ የሟችን የሞተበት እድሜ ታሳቢ በማድረግ አንድ ላይ በአንድ ጊዜ ክፍያው መፈፀም ይኖርበታል፤

14.8 ሟች በመሞቱ ምክንያት አመልካች የቀለብ ክፍያ ሊከፈለው የማይገባ ከሆነ የቀብር ማስፈጸሚያ እና የህሊና ጉዳት ካሳ ብቻ የሚከፈል ይሆናል፡፡

14.9 ለጉዳቱ መከሰት የተጎጂው አስተዋፅኦ ካለበት ይህንኑ ያገናዘበ የካሳ ድርድር መደረግ አለበት፡፡

## አንቀፅ 15

## <u>የእንሰሳት ጉዳት ካሳ ጥያቄ</u>

15.1 በእንስሳት ላይ ኤሌትሪክ አደጋ ደረሰ በሚል የሚቀርብ ቅሬታን የቅሬታ ኣጣሪ ቢሮው እና ኮሚቴው አስፈላጊውን ማስረጃ በማሰባሰብ ያጣራል፤

15.2 አደጋ በደረሰበት አካባቢ ለሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ የተደረገ ጥቆማ እና የተጣራ ምርመራ መኖሩን ያረጋግጣል፤

15.3 አመልካች የእንስሳው ባለቤት መሆኑን ማስረጃ፤ የእንሰሳው ምንነት ፤ያስገኝ የነበረው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ፤ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ አግባብነት ካላቸው ተቋማት ማስረጃ በማሰባሰብ ኮሚቴው ወስኖ ድርድሩን በርትዕ ያደርጋል፤

15.4የእንሰሳው ባለቤት የጥፋት አስተዋፅኦ ካለበት ይህንኑ ያገናዘብ የርትዕ የካሣ ድርድር ለማድረግ ጥረት ይደረጋል፡

15.5 የእንሰሳው ባለቤት ጥፋት ለመመዘን ተፈጻሚ ህጎችን መመርመር አስፈላጊ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 16

## <u>በንብረት ላይ የሚቀርብ ጉዳት ካሳ ጥያቄ</u>

16.1 ኮሚቴው በድርጅቱ ጥፋት ምክንያት ንብረት ወድሞብኛል የሚል ቅሬታ አቅራቢ ሲያጋጥመው ተገቢው ማጣራት እና የቴክኒክ ሪፖርት ከዲስትሪክት ኢንፎርስመንት ዳታ ፕሮሰሲንግ፤የፎረንሲክ ምርመራ ፤ ውድመቱ የደረሰበት አካባቢ ከሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ እና ሌሎች ተዛማጅነት ካላቸው ክፍሎች ማስረጃ ይሰበስባል፤

16.2 ኮሚቴው የወደመው ንብረት ባለቤትነት የቅሬታ አቅራቢው ስለመሆኑ የሚቀርበውን ማስረጃ እና በህጋዊ መንገድ የያዘው ስለመሆኑ በበቂ ሁኔታ በማጣራት ያረጋግጣል፤

16.3 በኤሌክትሪክ ሀይል መዋዠቅ ምክንያት የኤሌክትሮኒክስ እቃ ተቃጥሎብኛል የሚል ቅሬታ ሲኖር የተቃጠለው እቃ በባለሙያ ታይቶ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

16.4ኮሚቴው ለውድመቱ ኃላፊነት መውሰድ ያለበትን አካል በጥንቃቄ አጣርቶ ይወስናል፡፡

16.5 በኤሌክትሪክ አደጋ ምክንያት ቤት ውስጥ የተቀመጠ ገንዘብ ተቃጥሎብኛል የሚል ወይም ሌሎች ተአማሚነት የሌላቸው አቤቱታዎች ተቀባይነት የላቸውም፤

16.6 ኮሚቴው የካሳ ውሳኔ ድርድሩን በሚያካሂድበት ጊዜ ጉዳት ደርሶበታል የተባለውን ንብረት ወቅታዊ ይዞታ እና ቀሪ የአገልግሎት ዘመን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ሳልቬጅ ቫሊዩ (Salvage value) ይሆናል፡፡

16.7 ኮሚቴው የወደመ ንብረት የጉዳት ካሣ ውሳኔ ሲወስን ንብረቱ በመውደሙ ምክንያት የቀረ ገቢ ወይም ጥቅም ይታሰብልኝ የሚለውን የቅሬታ አቅራቢውን ጥያቄ አይቀበልም፡፡

16.8 . ጉዳት የደረሰበት ተሽከርካሪ ከሆነ የጉዳት ካሣው ሲወሰን የተሽከርካሪው የሥራ ዘመን፤ ሞዴል፣ ከመንገድ ትራንስፖርት የተሰጠ ፍቃድ የአገልግሎት ጊዜና ሳልቬጅ ቫሊዩ (Salvage Value) መሠረት በማድረግ ይወሰናል፡፡

## አንቀፅ 17

## በተቋሙ ሰራተኛ ላይ ለሚደርስ የስራ አደጋ የሚከፈል የካሳ ክፍያ ስሌት

17.1. አንድ ሰራተኛ ላይ አደጋ በሚደርስበት ጊዜ ከተቋሙ ክሊኒክ አቅም በላይ ካልሆነ በስተቀር ተቋሙ ውል ወደ ገባባቸው የጤና ተቋማት በመሄድ መታከም አይችልም፤

17.2. ጉዳት የደረሰበት ሰራተኛ የቅርብ ሃላፊ የደረሰው አደጋ ትክክለኛነትና በምን ሁኔታ አደጋው እንደደረሰ በኃላፊነት ማረጋገጥ ይኖርበታል፤

17.2. አደጋ የደረሰበት ሰራተኛ ተቋሙ ውል በያዘበት ህክምና ተቋም ለህክምና መላክ አለበት ፤

17.3. ጉዳት የደረሰበት ሰራተኛ ህክምና እንደጨረሰ የአካል ጉዳት ካለበት በሐኪሞች መማክርት ጉባኤ በፐርሰንት የመጣውን ጉዳት መሰረት በማድረግ ኮሚቴው ተገቢውን የካሳ ክፍያ በመመሪያው መሰረት ሰርቶ እንዲከፍል ሃሳብ ያቀርባል፤

17.4. ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ሰራተኞች በስራ ላይ ጉዳት ደርሶበት ህይወቱ ቢያልፍ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መሰረት የ60 ወር ደመወዝ ይከፈላል፤

17.5. ህይወቱ ያለፈው ተጎጂ ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች ወይም በቀን ስራ የተቀጠሩ የቀን ሰራተኞች ከሆኑ ሊከፈለው የሚችለው የካሳ ክፍያ ጣሪያ 100,000 ብር (አንድ መቶ ሺ ብር ) ይሆናል፤

17.6 ከላይ የተጠቀሰው አንቀጽ 17.5 እንደተጠበቀ ሆኖ ለተወሰነ ጊዜ እና ቀን ሰራተኞች ላይ የአካል ጉዳት ሲደርስ የካሳ ቀመሩ በህክምና ቦርድ የተረጋገጠው ጉዳት መጠን በፐርሰንት × 100 ሽህ ብር ሆኖ ይሰላል፡፡

17.7. ላልተወሰነ ጊዜ በተቀጠረ ሰራተኛ ላይ የደረሰው ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ከሆነ ሰራተኛው የአመቱ ደመወዝ በአምስት ተባዝቶ የሚያገኝ ይሆናል ፤

17.8 ለቀን ሰራተኛና ለተወሰነ ጊዜ ለተቀጠሩ ሰራተኞች ሊከፈል የሚችለው ከፍተኛው የህይወት ካሳ ወይም ዘላቂ የአካል ጉዳት ክፍያ 100,000 ሲሆን ሚች

ለሞቱ ምክንያት የእሱ ጥፋት/ አስተዋፅኦ/ ካለበት ካሳ ክፍያው እንደ ጥፋቱ መጠን በርትእ ተቀንሶ የሚከፈል ይሆናል፣

## አንቀፅ 18

## በሦስተኛ ወገኖች ምክንያት የሚደርስ አደጋን በተመለከተ

18.1. የቀረበው ቅሬታ በሦስተኛ ወገን ተሳትፎ ምክንያት ሲሆን ኮሚቴው ይህ ሦስተኛ ወገን የድርድሩ አካል እንዲሆን በህግ ክፍሉ በኩል ጥሪ ያደርግለታል፣

18.2. በቀረበው ቅሬታ ተሳትፎ ያለው ሦስተኛ ወገን በበኩሉ ለጥሪው ያለውን ምላሽ እና ማስረጃ ያቀርባል፣

18.3. ሦስተኛ ወገን ሙያዊ ጥፋት /ግድፈት የፈጸመ የድርጅቱ ሠራተኛ ሊያካትት ይችላል፣

18.4. በአንቀፅ 18(3) የተገለጸውን ሙያዊ ጥፋት ግድፈት ትርጓሜ ከተፈጻሚ የሀገሪቱ ህጎች እና ከፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2126 /3/ እና 2134 መሰረት ተገናዝቦ የሚፈጸም ይሆናል፣

18.5. ቅሬታው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በሦስተኛ ወገን ጥፋት ከሆነ በኮሚቴው በመጨረሻ ከተወሰነው ክፍያ በተጨማሪ ተቋሙ በድርድሩ ሂደት ወጪ ያደረገው በከፊል/በሙሉ ሶስተኛው ወገን ለተቋሙ ገቢ ያደርጋል፡፡

18.6. ቅሬታ አቅራቢዎች ሁለት እና ከሁለት በላይ በሚሆኑበት ጊዜ በድርድሩ አልሳተፍም ያለውን ወገን በመተው ከተቀሩት ቅሬታ አቅራቢዎች ጋር ድርድሩን ማካሄድ ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀፅ19

## የስምምነት ፎርም

የካሳ ድርድሩ አልቆ በመጨረሻ ክፍያ ሲፈፀም፡-

19.1 ለተጎጂ ክፍያ መፈፀሙን የሚያስረዳ ክፍያ የተፈጸመበት ቀን ፣ ቦታ

19.2 የአቤቱታ አቅራቢውን ሙሉ ስም እና አድራሻ ፣

19.3 ፤የደረሰውን አደጋና የቀረበው አቤቱታ ዝርዝር ፤

19.4 የተደረሰው ስምምነት እና የተከፈለው የካሳ መጠን በመግለፅ አቤቱታ አቅራቢው ካሳ እንደተከፈላቸው በመስማማት በፊርማቸው ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

## አንቀፅ 20

## የመመሪያው ተፈጻሚነት፤

23.1. ይህ መመሪያ በድርጅቱ ከፍተኛ ስራ አመራር ቡድን ታይቶ ከጸደቀበት ጊዜ አንስቶ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

23.2. ከዚህ በፊ.ት በደብዳቤ ቁ.68.4/182/06 በቀን ነሀሴ 29/2006 ዓ/ም የካሳ ክፍያ አፈፃጸምፖሊሲና ፕሮሲጀር /Ethiopian electric utility public liblity and self insurance procedure / በሚል ርእስና በሶስተኛ ወገን ረገድ /third party cover /ላይ ወጥቶ የነበረው መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## አንቀፅ 21

## የመመሪያው ስለመሻሻል

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በድርጅቱ ከፍተኛ ስራ አመራር ቡድን ሊሻሻል ይችላል፡፡

ሺፈራው ተሊላ

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና ስራ አስፈፃሚ